# ለትግል አንድነት ጥሪያችን - በአርአያነታችን!!

በግንቦት 97 ምርጫ ሳቢያ የኢትዮጵያ ህዝብ በሚልዮን እየተቆጠረ የተንሳቀሰው አንድን መንግስት በፈለገውና ባሻው ሌላ መንግስት ለመተካት ብቻ አልነበረም። ህልማችን በድህረ ግንቦቱ ወቅት የነበረው የዴሞክራሲ ፍንጭ ሰፍቶና ስር ሰዶ ሃገራችን ሰብአዊ መብቶች ያለ አንዳች መሸራረፍ የሚከበሩባት፤ የህግ የበላይነት በተገዥዎች ላይ የሚጫን የገዥዎች መፃደቂያ ሳይሆን በሁሉም ተከብሮና ተረጋግጦ አገራችን በተጠያቂ መሪዎች የምትመራበት ስርአት ለመፍጠር፤ ለዘመናት ህብረተሰባችንን ሲያደማ ከቆየው የአመፅና አሸናፊ/ተሸናፊ አዙሪት ወጥተን በብሄራዊ እርቅ ፖለቲካ የተረጋጋ ህብረተሰብ ለመፍጠር፤ በእኩልነት፤ በወንድማማችነትና በትግግዝ መንፈስ ከብረት ጠንክሮ ለሚገነባ የሃገር አንድነት መሰረት ለመጣልና በነዚህ ሁሉ እሴቶች እውንነት ተመርኩዞ ህዝባችን ለዘመናት ተውተብትቦ ከሚማቅቅበት የጥፋት አዙሪት ለአንዴም ለዘላለሙም ተላቆ ወደ አገር ግንባታና ልማት፤ ወደ ማህበራዊ ፍትህና ብልፅግና ያተኮረ ህብረተሰብ የመገንባት ህልምና ተጋድሎ ነበር።

ይስፋኑ፤ ይዳብሩ እንላቸው የነበሩት ሰላምና ዴሞክራሲ ዛሬ ከድህረ ግንቦቱ ወቅት ይልቅ ከነ ጭራሹ ደብዛቸው እየጠፋ ነው። በድህረ ግንቦቱ ወቅት በቋፍ የነበረው ነፃ ፕሬስ ዛሬ ሽታውም የለ። በድህረ ግንቦቱ ዘመን "በተራ" የአፈና አገዛዝ ተሰማርተው የነበሩት ጥቂቶች ዛሬ በሽብር ብቻ ለመግዛት የተገደዱበት ደረጃ ደርሰዋል። በድህረ ግንቦቱ ወቅት የነበረችው የተጠያቂነት ፍንጭ መንምና ወጣቶች በደርዘን ሽህ እየታፈሱ ቁጥራቸው፤ መድረሻቸው፤ የሚፈለጉበት ወንጀል በውል ባልታወቀበት ሁኔታ በየማጎሪያ ጣቢያ መወርወራቸው ቀጥሉዋል። ወላጆች ቢያንስ ልጆቻችንን የት እንዳደረሳችኋቸው ንገሩን ብለው ለሚያሰሙት እሮሮ ጆሮ ዳባ ልበስ ተብሎ በሰኔና በጥቅምት ለተፈፀመው ግፍ ምንም እልባት ሳይገኝ ሌላ የወጣቶች አፈሳ ዙር እየተካሄደ ነው። በሃገራችን ታሪካዊ ተገቢነት ያለውን የብሄሮች እኩልነትና ወንድማማችነትን ጥያቄ ድሮም ቢሆን ለመነገጃ ሲጠቀሙበት የቆዩት የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች አሁን ደግሞ በፋሽሽታዊ ግፍ አፍነው የያዙትን የትግራይ ህዝብ ከተቀረውና ወንድሙ ከሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ነጥለው ለማናከስ ሃፍረትም ይሉኝታም በማያውቅ ፕሮፓጋንዳ ሲንቀሳቀሱ እየታዘብናቸው ነው። ይህን ሁሉ ስናይ የምንደርስበት አንድ መደምደሚያ ብቻ ነው። በእርግጥ ኢትዮጵያችን ከዛሬ አመት ዛሬ በየአቅጣጫው ወደኋላ እየሄደች ትገኛለች።

ይህ የህዝባችን የአተርፍ ባይ አጉዳይ ሂደት ግን ምንም ዘላቂነት የለውም። የግንቦት አንቀሳቃሽ እሴቶች ሚልዮኖች ያነገቡዋቸውና ሊታገሉላቸው ሊሰውላቸው የቆረጡባቸው እሴቶች በመሆናቸው፤ በአለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን ሁሉም ቆሜላቸዋለሁ የሚላቸው በመሆናቸው ይህ የኋሊት ጉዞ በጣም ጊዜያዊ ክስተት ነው። በአፈና አገዛዝ ላይ የተነሳን ህዝብ በሌላ ተጨማሪ አፈና፤ መብታችን ብለው የተነሱ ሚልዮኖችን በለየለት አመፅና በሽብር ተቋቁሜ ድል አደርጋለሁ የሚለው የፀረ ህዝቦች ቅዠት ነው። አይሰራም። ቢሰራ ኖሮ እስከዛሬ ማንም ህዝብ በየትም አገር ምን ጊዜም ቢሆን ታግሎ ነፃነቱን የሚጎናፀፍበት ምንም ተአምር አይኖርም ነበር። የቆረጡ ሚልዮኖችን ፀረ አፈና ህዝባዊ ትግል በጥቂቶች አፈና ብርታት ለመቋቋም መሞከር እሣን ውሃ ውስጥ አሰምጣለሁ ብሎ እንደመግደርደር ያህል ከንቱ መፍጨርጨር ነው።

ከሰኔ ወር ጀምረን በተጨባጭ የምናየው እውነታ ይኸው የግፍና የትግል ተያይዞ የማየል ሂደት ነው። ጭፍጨፋ የሚልዮኖችን ህዝባዊ ትግል ይገታ ቢሆን ኖሮ ተጋድሎዋችን በሰኔው ፀረ ህዝብ አመፅ ማግስት ባከተመ ነበር። ይህ አልሆነም። ሰኔ ጥቅምትን ወለደ። ይህንንም በደም አጥለቅልቀን እንወጣዋለን ያሉት ጥቂት ፀረ ህዝቦች እንደገና የንፁሃን ደም በግፍና በገፍ እንዲፈስ አደረጉ። እንደተመኙት ህዝባችን አልተንበረከከላቸውም። ህዝባዊው ተጋድሎ ከታህሳስ ጀምሮ እንደገና አገረሸ። ዛሬ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች መጠን የሳተ አመፅ በህዝባችን በተለይ በወጣቱና በተማሪው ላይ ላይ እንደገና እየወረደ ነው። ይህም አይሰራም። የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ገባቸው አልገባቸው፤ ተቀበሉት አልተቀበሉት ትጥቅ ያስፈቱ እየመሰላቸው እያበራከቱ የሚሄዱት ግፍና አፈና ከድጥ ወደ ማጥ ጉዞ ስለሚሆንባቸው በየእለቱ ይበልጥ ታጋይ እየፈለፈለ እስከ መጨረሻው ድል የሚቀጥል ህዝባዊ ትግል መቀስቀሱ አይቀሬ ሂደት ነው።

ወጣቱና ተማሪው በቃኝ፤ ተንገሸገሽኩ፤ አሻፈረኝ ብሎ በያለበት መነሳሳት መቀጠሉ የጥቂቶች "ሴራ" አይደለም። ማንም ሊገታው የማይችል የአኩሪው ኢትዮጵያ ተማሪዎችና ወጣቶች ንቅናቄ ቅርስ ግፊት ነው። ይቀጥላል። እናት አባት ልጆቻቸው በደርዘን ሽህ እየተቆጠሩ ደብዛቸው ሲጠፋ "የት ደረሱ" ብለው እነሱም በደርዘን ሽህ እየተንቀሳቀሱ መጠየቃቸው አይቀሬ የወላጅ አንጀት የሚጠራው ተፈጥሮዋዊ ግዴታ ነው። ዛሬ ሁሉም ቤቱን ዘግቶ ቢያለቅስ ነገ ሁሉም በአንድ ላይ ተነስቶና አደባባይ ወጥቶ ወንጀለኞቹ ተጠያቂ እንዲሆኑ ይጠይቃል። ለጅምላ መቃብር የተዳረጉትም ዜጎቻችን "በሹም የታዘዘ" አፈር እንደለበሱ አይቀሩም። በመቶ ሽህ የሚቆጠር ዘመድ አዝማድ በያለበት ከተጣሉበት አንስቶ በክብር ለማሳረፍ መንቀሳቀሱ በባህላችን የቅዱስ ቅዱስ የሚባለው የእርም የማውጣት መብት የማስከበር ጉዳይ ስለሆነ ምንም አይነት ፀረ ህዝብ አመፅ ሊገታው አይችልም። ተቃዋሚ ደግፈሃል በሚል ውንጀላ ነጋዴው ሱቁ ሲታሸግ፤ ታክሲ ነጅው ፈቃዱን ሲቀማ፤ ጎዳና ተዳዳሪው ወጣት ድህነቱና እድሜው ከወንጀል ተቆጥረውበት ከያለበት ሲታፈስ፤ ሰራተኛው ስራ ማቆም አድማ ተሳትፈሃል ተብሎ ከስራው ተፈናቅሎ ከነሚስቱ ከነልጆቹ ጉረሮው ሲዘጋ....ይህ ሁሉ ከመብትም ከዴሞክራሲም ከሃገር ክብርም አልፎ የህልውና ጥያቄ አፍጦና አግጦ እንዲቀርብ ያደርገዋል። ይህ ደግሞ ከወያኔ/ኢህአዴግ ግፍ ጋር ተያይዞ እያየለ የሚሄድ የተቃውሞ ትግል መቀስቀሱ ሳይታለም የሚፈታ ጉዳይ ነው። የነፃው ፕሬስ ማበብ፤ የተጠያቂነት መስፈን፤ የሰብአዊ መብቶች መከበር፤ የህዝቦች ወንድማማችነት መለምለም የመሰሉ ቁምነገሮችን እያነሳ ለአስራ አምስት አመት በውጭም በውስጥም ሲዋደቅ የቆየው ዴሞክራትና አገር ወዳድ በሚልዮን የሚቆጠር ሃይል ነው። ይህ ታጋይ ሃይልም ቢሆን አነሰ ያለው ሲቀነስበት እንቅስቃሴውን ማፋፋሙና መቀጠሉ ዴሞክራትነቱ፤ አገር ፍቅሩ፤ በህዝብና በታሪክ ፊት አለብኝ የሚለው የሃላፊነት ስሜቱ የሚጭንበት ግዴታ ነውና ትግሉ ይቀጥላል።

መጭው ጊዜ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች በዚህ መልክ በሃገር ውስጥ በህዝብ ትግል ከእለት እለት ከወር ወር ይበልጥ እየተጨነቁ የሚሄዱበት ወቅት ብቻ አይደለም። ከድጡ ወደ ማጡ እያሉ የተያያዙት የጥፋት ጉዞ በአለም አቀፍ ደረጃም ይቀጥላል። ጥቂቶች በሃገራችን ላይ የተከሉት የወስላቶች ዴሞክራሲ ከአስራ አራት አመት መመፃደቅ በኋላ በመላው አለም ህዝቦች ፊት እርቃኑን ቆሞ መታየት ጀምሩዋል። የክስረትና የውርደት ሂደታቸው ምርጫ አይን ባወጣ ሁኔታ ሲያጭበረብሩ በተከሰተው ወገዛ ተከፈተ። ሰኔ ላይ የህዝብ ድምፅ ይከበር ብሎ በተነሳው ህዝብና በተለይ በወጣቱ ላይ ባደረሱት ግፍ ከየአቅጣጫው ተወግዘው ለአሳዳሪዎቻቸው አሳፋሪ መሆን ጀመሩ። ጥቅምት ላይ በሌላ የግፍ አዙሪት ተሰማሩ። ትላንት "አዲስ የዴሞክራሲያዊ መሪዎች ትውልድ" እየተባሉ ይሞካሹ የነበሩትን እነመለስ ዜናዊን የውጭው አለም ከእንግዲህ ከተራ ወገዛ አልፎ ይጠየፋቸው ጀመረ። አራት መቶ ሚልዮን የሚጠጋ ህዝብ የሚወክለው የአውሮፓ ፓርላሜንት ያሳለፈው ውሳኔ ባለፉት አመታት እንደለመድነው የሰብአዊ መብቶችን ረገጣ በማውገዝና የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ በመጠየቅ አያቆምም። የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ከህዝብ ዘርፈው በውጭ ባንኮች ያስቀመጡት ገንዘብ እንዲከበር፤ እነሱም ቢሆኑ ከእንግዲህ በአውሮፓ ህብረት አባል በሆኑ ሃገሮች ድርሽ እንዳይሉ ቪዛ እንዲከለከሉ፤ ባለፉት ወራት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ስለለተፈፀመው ግፍ በተመድ አቀነባባሪነት አንድ አጣሪ ኮሚሽን እንዲቋቋም፤ ስለታሰሩትና ስለተገደሉት ዜጎች የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ይፋና ዝርዝር መግለጫ እንዲሰጥ ወዘተ .....የሚጠይቅ ውሳኔ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የአለም ባንክና የአውሮፓ ህብረት በጋራ በወሰዱት ፀረ ወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች እርምጃ እስካሁን ለበጀት ማሟያ እየተባለ ለነአቶ መለስ መንግስት በየአመቱ በቀጥታ ይሰጥ የነበረው 375 ሚልዮን የአሜሪካን ብር እንዲቋረጥና ለህዝቡ የሚያስፈልገው ይህ ገንዘብ በሌሎች ይበልጥ ተአማኒነት ባላቸው ወገኖች አማካኝነት ወጭ እንዲደረግ መወሰናቸው ተነግሩዋል።

በውስጥም በውጭም ይህ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት አይከስሩ ክስረት ብቻውን የነፃነታችንን ዋዜማ አያበስርም። ከፊታችን ገና ብዙ ትግልና መስዋእትነት ይጠብቀናል። የወያኔ/ኢህአዴግን መሪዎች የሚጨብጡት አሳጥቶ የሚያናክሳቸው ህዝባዊ ትግል ከእንግዲህ ይበልጥ ተቀነባብሮና ተፋፍሞ በሃገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በውጭ አገሮች መቀጠሉ ወሳኝ ነው። ይህንን ታሪካዊ ተጋድሎ አስተባብረውና አቅጣጫ ሰጥተው ለድል ለማብቃት በመዋደቅ ላይ የምገኙ የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ስብስቦች ተማሪው ሆነ ነጋዴው፤ ታክሲ ነጅው ሆነ ምሁሩ፤ ገበሬው ሆኖ

ሰራተኛው፤ ወጣቱ ሆነ አዛውንቱ ተራ በተራ እየተነሱ ተራ በተራ በወያኔ/ኢህአዴግ ከሚጠቁበት ሂደት ይልቅ ሁሉም በአንድነት ለአንድ የጋራ አላማ እየተነሳ እንዲታገል በተደጋጋሚ ጥሪ ሲያደርጉ ቆይተዋል። በእርግጥም የህዝባችን ተጋድሎ ከአስከፊ ሸንፈት ተርፎ ለኢትዮጵያችን አዲስና ብሩህ ምእራፍ የሚከፍተው በትግል አንድነት ብቻ ነው። ይህ ተደጋጋሚ ጥሪ አጉል ልፈፋ እንዳይሆን የሚፈልጉ ግንባር ቀደም ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ህዝባችንን ለትግል አንድነት ሲጠሩ መጀመሪያ ራሳቸው ይህንን የትግል አንድነት ፈጥረው በአርአያነት መታየት ይኖርባቸዋል። ግንባር ቀደም ሃይሎች ተበታትነው አንዱ ወደ አራምባ ሌላው ወደ ቆቦ እያመላከቱ እዛው በዛው ደግሞ ህዝብን በአንድነት እንዲታገል የሚደረግ ጥሪ ከአንገት በላይ የሚደረግ ምንም ተአማኒነት የማይኖረው አካሄድ ሆኖ ይቀራል። ይህንን የትግል አንድነት ለመፍጠር ከተፈለገ ደግሞ የህብረታችን ውሳኔ በትክክል እንዳስቀመጠው ዛሬ የተያያዝነው ተጋድሎ የዚህ ወይም የዚያ የፖለቲካ ድርጅት፤ የዚህ ወይም የዚያ የሲቪክ ስብስብ፤ የዚህ ወይም የዚያ ግለሰብ ጉዳይ ሳይሆን በጠቅላላው በህብረተሰባችን ውስጥ ያሉ የፖለቲካና ሲቪክ ሃይሎች፤ የወጣቶች፤ የነጋዴዎች፤ የሴቶች፤ የወላጆች፤ የተማሪዎች፤ የሰራተኞች፤ የገበሬዎች፤ የምሁራን፤ የዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች የጋራ ተጋድሎ እንደሆነና ዛሬ ባለንበት ወሳኝ የትግል ምእራፍ ጠባብና ወገናዊ ድርጅታዊ አጀንዳዎችም ሆኑ ስሌቶች ቦታም ትርጉምም እንደሌላቸው ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል።

የህብረታችን ሁለተኛ አስቸኳይ ጉባኤ ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት አንድነታችሁን አጠንክራችሁ ትግሉን አፋፍሙ ለምንላቸው ወገኖቻችን እኛ ራሳችን በምሳሌነታችን አመራር መስጠት የሚያስችለን ሁሉን አቀፍ ጉባኤ በአስቸኳይ እንዲጠራ የሚጠይቅ ታሪካዊ ጥሪ አስተላልፏል። ይህ የኢዴሃህ ጥሪ ብቻ አይደለም። ግፉ በቃን፤ ድምፃችን፤ መብታችን፤ ህልውናችን ይከበር ብለው ለወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች እብሪት በየእለቱ የደም፤ የእንባ፤ የእስራት፤ የግርፋትና የወከባ ግብር እየከፈሉ ለወራት ትግሉን ህያው አድርገው የጠበቁትና ዛሬ ከአስከፊ ሽንፈት ለመትረፍ የአመራር ያለህ እያሉ በመጮህ ላይ ያሉ ሚልዮኖች ጥሪ ነው። ይህንን የሚልዮኖች ጥሪ እውን ለማድረግ በህብረቱም ሆነ በቅንጅቱ የተካተቱ ህዝባዊ ትግሉን ለመቀጠል የቆረጡ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች፤ የነዚህ ድርጅቶች የድጋፍ ኮሚቴዎች ተጠሪዎች፤ ኦነግን ጨምሮ የሌሎች ፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች፤ የመምህራን፤ የጋዜጠኞችና ሌሎች የሲቪኩ ማህረሰብ ስብስቦች፤ እንደዚሁም በያለበት "የህዝብ ድምፅ ይከበር" ብለው በመዋደቅ ላይ ያሉ የዜጎች ኮሚቴዎች በአስቸኳይ ተገናኝተውና መክረው ላለንበት የቀውስ ወቅት የሚመጥን የጋራ ስትራቴጂ የሚነደፍበትንና ለዚህም ተግባራዊነት አንድ የጋራ ትግል አካል የሚቋቋምበትን ዘዴ ማመቻቸት ይዋል ይደር የማይባል አገራዊ ግዴታ ነው።

ድል በጋራ ትግል
የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት